# ትብብር ከማን ጋር? ዓላማውና ልዕለ-ግቡስ?

## ኢትዮጵያን ለማዳንና ሕዝቧን ለመታደግ ኢትዮጵያዊ አስተሣሰብንና እምነትን ይጠይቃል!

*(ክፍል አምስት - ካለፈው የቀጠለ)*
*ከአያልሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት ( ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፪ ሀሽ ፫ ዓ/ም)*

በተገቢ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ግን የቀረው ለውጥ ፈላጊ ክፍል በአገራችን በብሔራዊ እርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ሂደት በማድረግ ፍትኅንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን እየታገለበት እንዳለውና በሚያልመው መልክ ሣይሆን እነዚኽ ኃይሎች ችግሮቻችን ናቸው ብለው የሚታገሉባቸውን ዓላማዎች በአገሪቱ **ማዕቀፍ ሥር መፍታት እንችላለን የሚል እምነትም፣ አስተሣሰብም ሆነ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ነው::** ለችግሮቻችን ተጠያቂ የሆኑትን የተበላሹ ሥርዓቶች በጋራ ታግለን፣ በቡድን ይሁን በአጠቃላይ በአገሪቱ ዜጎች ላይ ከአሁን በፊት የደርሱም ሆነ በቀጣይነት እየደረሱ ያሉ በደሎች እንዳይደገሙ በሚደረገው የጋራ ትግል አስፈላጊው ዋስትና ተሰጥቶና እኩልነት ተረጋግጦ ከቀረው የአገሪቱ ሕዝብ ጋር ተቻችሎ፣ ተከባብሮና ተደጋግፎ የመኖር ዓላማም ሆነ አጀንዳ በነዚኽ ድርጅቶች ዘንድ የለም:: ስለዚኽ ከእነዚኽ ኃይሎች ጋር መተባበር 'መቻቻልን' ያመጣል የሚለው አባባል ከንቱ ምኞት ነው:: **እነሱ በያዙት ፍልሥፍና የሚመሩ ድርጅቶች "የበለጠ አክራሪ" እንዳይሆኑ ሊያደርጋቸው የሚችል አንድም "ቆመንለታል" የሚሉት ሕዝብ ሙሉ መብቶቹ ተከብረውለትና እኩልነቱ ተረጋግጦለት ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር የተረጋጋ ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖር ሲደረግ፣ አለያም በእነሱ ላይ የኃይል ሚዛን ሲያይል ብቻ ነው::** ሁለተኛውን ለጊዜው እንተወውና የአገር-ወዳድና የዴሞክራት ኃይሉ ትግል ደግሞ የመጀመሪያው እውን እንዲሆን ነው:: ያ ደግሞ እውን እንዲሆን ከማይፈልጉ ክፍሎች መኻል እነዚሁ ኃይሎች ዋናዎቹ ናቸው:: ስለ-ሆነም ነው እነኝኽን በፍልሥፍናም ይሁን በልዕለ-ግብ አብረው የማይሄዱ ኃይሎችን አቅፎ ያንን የጋራ የፍትኃና የእኩልነት ትግል እውን ማድረግ የሚያስቸግረው::

መ) *"እነዚኽ ኃይሎች ጋር ከአሁኑ አብሮ መሥራት ካልተጀመረና አብረናቸው እንደምንሠራ ካላረጋገጥንላቸው እንደ-ገፋናቸው ይቆጠራል፣ በኋላም ወያኔ ሲወገድ ማቅረብ አይቻልም"፦* ይኽም እንዲሁ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ምኞታዊና የተሣሣተ አስተሣሰብ ላይ ያረፈ ስሌት ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ እነዚኽን ኃይሎች ይዞ የአገራችንንና የሕዝባችንን ዘለቄታዊ ጥቅሞች ባስጠበቀ ሁኔታ አገዛዙን ለመጣል የማይሆን ነው:: ስሌቱ ምናልባት በአንድ በኩል ቡድኖቹን በስሙ የሚንቀሣቀሱበት ወገናችን ሕጋዊ/ብቸኛ ተወካይ አድርጎ ከመቁጠር የመነጨ ሊሆን ይችላል:: የሚገርመው ይኽንኑ አሣብ የሚያቀነቅኑ ወገኖች፣ ቢያንስ በይፋ እንደሚሉት ከሆነ፣ በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ አይወክልም ይላሉ:: አዎን በእርግጥም አይወክልም:: ለሕወሓት "የተነፈገ" "የሕዝብ ተወካይ" መሆን እንዴት ለነዚኽኞቹ ቡድኖች እንደሚሠራ ግን አይገባኝም::

እንደሚታወቀው እነዚኽ ኃይሎች እስከ-አሁን በተሞከሩ የጋራ ትግል ጥረቶች ላይ ተሣታፊ እንዲሆኑ እንጂ በዴሞክራሲና የአንድነት ክፍሎች እንዲገለሉ የተደረገበት ጊዜ የለም:: በአብዛኛው እራሣቸውን ከቀረው የለውጥ-ፈላጊ ጎራ ወጣ አድርገው ማየት ስለሚፈልጉና "በኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባንም" ከሚል አስተሣሰብ ላይ በተመረኮዘው አቋማቸው ምክንያት ግን የመተባበር ፈቃደኝነት ያልታየው በእነሱ በኩል ነው:: ስለ-ሆነም "መግፋት" የሚለው ቃል ምናልባት እነሱኑ የሚመለከት እንጂ የአንድነት ኃይሉን የሚመለከት አይሆንም:: ለዚኽም ነው ካለፈው የረጅም ጊዜ ልምድና ከድርጅቶቹ ተፈጥሮአዊ ባኅሪ አኳያ ወደ-ማባበል ወይም ሽንገላ የተሸጋገረው አካሄድ እነሱ እራሣቸውን ከቅጥ በላይ አግዝፈው እንዲያዩ ከማድረግና የሚደረግን ትብብር የእነሱ አጀንዳ ማሚያ እንዲሆናቸው በቀጭኑ ከማሰብ ውጭ ስለማያዩት ለጋራው ትግል ጠቀሜታ ያለው ውጤት አይኖረውም፣ ጨርሶም አይጠቅምም፣ አልፎም አደገኛ መዘናጋት ነው የምለው::

እነኝኽ ቡድኖች ድኅረ-ወያነ/ኢሕአዴግ ለሚኖረው ሁኔታ አቋማቸውን አስተካክለው ከቀረው ወገናቸው ጋር ለሁሉም የሚጠቅምና ሁሉም አትራፊ የሚሆንበት ሥርዓት በማስገኘቱ ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው ከተፈለገ ወይም ከታሰበ ጊዜው ከአሁኑ የያዙት አቋም "ቆመንለታል" ለሚሉት ወገናችን እኩልነትንም ሆነ ፍትኅን እንደማስያገኝ እንዲገነዘቡ ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው:: ከወዲኹ መሠረታዊ በሆኑ የጋራ ዕድልን በጋራና በኢትዮጵያ አገራዊ-ማዕቀፍ ሥር ሊፈቱ እንደሚችሉና እንደሚገባ ማመን ያልቻሉ፣ አሁን በሚደረገው 'የሌላው' ድጋፍ "የእኔ" በሚሉት አካባቢ ከተቆናጠጡ በኋላ ድኅረ-ኢሕአዴግ ለምና እንዴትስ አቋማቸውን ይለውጣሉ ተብሎ የግርንቢጥ እንደሚታሰብ ጨርሶ አይገባኝም:: ወደ-መኻል የሚያመጣቸው አቋም ሊወስዱ ከቻሉ ከወዲኹ እንጂ በኋላማ ጭንቀታቸው የሚሆነው ከደረሱበት ተነስተው ወደ-ተቋቋሙበትና

ወደ-ታገሉበት ግባቸው ስለሚወስዳቸው፣ “የእኛ” በሚሉት ምድር ላይ ያላቸውን ፍፁም የበላይነት ስለሚያረጋግጡበት፣ ወዘተ.. ሁኔታ እንጂ ሌላ አቅጣጫ ስለ-መያዝ ሊሆን የማይችል ነገር ነው:: ከወዲኹ ግን አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ እንኳን ባይሆን ቆም-ብለው እንዲያስቡ የሚረዳቸው በቅድሚያ የአንድነት ኃይሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መርኅን የተከተለ የጋራ አቋምና አሠላለፍ መያዝ ሲችል ነው:: ስለዚኽ የሚጠፋ ጊዜ ካለ በዚሁ ጥረት ላይ ሊውል ይገባል እላለሁ::

ሠ) *“ከነሱ ጋር አብሮ መታገሉ አገር-አቀፍ ብሔራዊ መግባባት እንዲኖርና ዴሞክራሲ እንዲያብብ የተሻለ ሁኔታን ይፈጥራል”*:- ቀደም-ሲል ለመግለጥ እንደ-ሞከርኩት የአሁኑ “የትብብር” ጥረት በማያሻማ መልክ የሚጠቅመው እነዚኽን ፀረ-አንድነትና ተገንጣይ ክፍሎች ነው:: በእግዚአብሔር፣ ከወዲኹ የየራሱን አጥር አጥሮና በጋራው ጉዳይ አያገባኝም ብሎ የቆመን ድርጅት ከወዲኹ አንፃራዊ ድክመት ላይ በሚገኝበት ጊዜና “የእኔ” በሚለው የአገሪቱ ክፍል እግሩን መትከል ባልቻለበት ወቅት ስለ-ጋራ የወደፊት ዕድል ከቀረው ዴሞክራት የአንድነት ኃይል ጋር በራሱ መሥፈርት ካልሆነና የቆመበትን ጠባብ አጀንዳ ያራምድልኛል ብሎ ካላመነ ደፍሮ አብሮ መሥራት የማይፈልግ ክፍል፣ ነገ “የኔ” በሚለው ቦታ ላይ ኅልውናውን በገሃድ ማረጋገጥ ሲችል የባሰ “በክልሌ” አትድረሱብኝ ከማለት ውጭ የተለየ ሊያደርግ ይችላል ብሎ ማሰቡ የፖለቲካ ብስለት የጎደለውና ሲበዛም የዋህነት ከመሆን ሌላ ትርጉም ይኖረዋል?

**ብሔራዊ መግባባት ሊመጣ የሚችለው ቃሉም እንደሚያመለክተው ብሔራዊ አስተሣሰብን ወይም ሁሉም 'የእኔም የጋራም ነው' በሚለው አንድ የመልክዓ-ምድር (ጂኦግራፊ) ክልል ሥር የጋራ ዕድል እንዳለው ማመንና መቀበልን የግድ ይላል:: አንዱ ክፍል አገሩን በጋራ በሚጋራው ብቻ ሣይሆን በዜጋ ወገኑ “ቅኝ ተገዥ ነኝ፣ ጠላቴ ነህ፣ በጉልበት አስለቅቅሃለሁ” ከሚለው ጋር አብሮ የመኖር ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት በሌለበት ሁኔታ ብሔራዊ /አገራዊ መግባባት ማስገኘት እንዴት እንደሚሆን ይቸግረኛል:: ቅድሚያ ሊሆን የሚገባው እነዚኽ ክፍሎች በዚያች የሁላችንም በሆነች አገር ውስጥ ፍትኅንና እኩልነትን ከሚነፍጉ ኋላ-ቀርና ጨቋኝ ሥርዓቶች ሌላ ጠላት እንደሌላቸው ማሣመን ነው:: ያ ደግሞ ወገናቸውን፣ አገራቸውንና የአገራቸውን አንድነት እንደ-ጠላት እንዲያዩ ከሚያደርግ የፖለቲካ ፍልሥፍናና አደረጃጀት መላቀቅን ይጠይቃል:: የሆነ-ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ከነዚኽ ኃይሎች ጋር “መተባበር” ለብሔራዊ መግባባት ይረዳል የሚለው አባባል ጉም-ጨባጭ ነው:: ልዩነትን የኅልውናው መሠረት ያደረገ አስተሣሰብና አደረጃጀት ላይ ተቆሞ ብሔራዊ መግባባት ማስገኘት አጉል ምኞት ነው::**

ስለ-ሆነም ከሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ቀጥሎ በአገራችን ብሔራዊ መግባባት-አስገኚ ሂደትን ለመከተል እንቅፋት ከሆኑት ዋና-ዋና ክፍሎች መኻል እነዚኽ ልዩነትን የኅልውና መሠረት ባደረገ አስተሣሰብ የተደራጁና የሕዝብን አንድነት የሚፃረሩ ኃይሎች እንደሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: ሕወሓት/ኢሕአዴግም ሆነ እነዚኽ ኃይሎች ከምንም በላይ የሚፈሩትና የማይጥማቸው የሕዝብ አንድነት ነው:: ኢትዮጵያውያን ጎሣ/ብሔረሰብ-ዘለል አደረጃጀትን ሲከተሉ፣ ከልዩነት ይልቅ ለአንድነታቸው ቅድሚያን ከሰጡ፣ እንደ-አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ጋምቤላ፣ ሃድያ፣ ወዘተ.. ሣይሆን እንደ-ኢትዮጵያዊ ሲያስቡ፣ ሲቆሙና ሲሰለፉ እነዚኽ ቡድኖች ኅልውና አይኖራቸውም:: ስለየ-ቋንቋ ምድባችን ወይም ብሔረሰባችን ሣይሆን አንደ-ኢትዮጵያዊ ዜጋ እናስብ ሲባል “የብሔረሰብ መታወቂያየን ለመደፍጠጥ፣ ባህሌን 'ለሌላው' ተገዥ ለማድረግ፣ ወዘተ..” ነው የሚል ሥጋትም ጥርጣሬም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ሊኖር ይችላል:: እንዳልሆነ ግን ያውቁታል፣ ወይም ሊረዱት ይገባል::

አንደኛ ለኦሮሞው ኦሮሞነትን፣ ለትግሬው ትግሬነትን፣ ለወላይታው ወላይቴነትን፣ ለአማራው አማራነትን፣ ወዘተ... ማንም ሊቀማውም ሆነ ሊቸረው አይችልም:: አንጡራ ሃብቱ ነው:: ኢትዮጵያዊነት ኦሮሞነትን፣ ኦጋዴናዊነትን፣ ሐድያነትን፣ ወዘተ አይሽርም፣ አይፃረርም:: በአንዳንድ ጠባብ ቡድኖች እምነትና አካሄድ ከሆነ ግን እነኝኽ የቋንቋ ምድቦች ወይም ብሔረሰቦች ኢትዮጵያዊነትን ሊነፈጉ ይችላሉ:: ስለዚኽ ትግሉ እንደዋዛ ልናጣው በምንችለው፣ ለኅብረተሰባችን መረጋጋትና ለሰላም፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ እውን መሆን፣ ለጋራ እድገትና ብልፅግና ዋስትና፣ የጋራ ጥሪታችን በሆነው ኢትዮጵያዊነት ላይ መሆኑ ተገቢ ነው እላለሁ::

ሁለተኛ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ባህሎቻችን ሁሉ የሁላችንም ቅርሶችም ቋሚ ሃብቶችም ናቸው:: ማናቸውም የማንም የበላይም ሆነ የበታች ሊሆኑ አይችሉም:: ሁሉንም ባህሎቻችንና ቋንቋዎቻችንን መንከባከብና ማሳደግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው:: ዴሞክራሲ በልዩነት ተቻችሎና ተከባብሮ መኖር መቻልን ይጠይቃል:: ታዲያ በኅብረተሰብ መኻል ያሉ ልዩነቶችን የኅልውናው መሠረት ያደረገና የልዩነት አጥር-አጣሪ ኃይል በልዩነት ተቻችሎ መኖር እምነት ጋር አይተዋወቅም:: ምክንያቱም መቻቻል ካለ ኅልውና አይኖረውም:: ስለ-ሆነም በአገራችን ብሔራዊ መግባባት እንዲኖርና ዴሞክራሲ ሥር እንዲሰድ ከተፈለገ አሁን የተያዘውን ዓይነት አግላይ ፍልሥፍናን የሚከተሉ ቡድኖች እንዲጠናከሩ የሚያደርግ እርምጃ መውሰዱ ትርጉም የለውም::

ረ) *“ከነዝኽ ኃይሎች ጋር መሥራት አለ-መፈለግ ወደ-ፊት ያዬ ሣይሆን ወደ-ኋላ ያየ ነው። ከአሁን በፊት ስለ-ተደረጉ ነገሮች የምንነጋገርበት ጊዜ አሁን አይደለም፣ ይኽንን የሚተቹ የተሻለ አማራጭ ማቅረብ ያልቻሉ ክፍሎች ናቸው”፡-* ይኽ ደግሞ “ያለፈውን ያላስተዋለና የዘነጋ ውድቀቱን ያመቻቻል” የሚባለውን ያስታውሰናል። አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን በዚኽ አካሄድ ላይ ያላቸው ተቃውሞ በምናልባታዊነት ላይ የተመሠረተ፣ ባዶ ጭንቀት የወለደው አጉል ስጋትም ይሁን በነዚኽ ቡድኖች ላይ አስቀድሞ ካለ ያጠየመ አመለካከት የመነጨ ወይም አንዳንዶች በግልቡ ሊያስቀምጡት እንደሚከጅሉት “ከአክራሪ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛነት” አልፎም ከ“ትምክህተኝነት” ስሜት የተፈጠረ አይደለም። ከድርጅቶቹ መሠረታዊ ዓላማና አቋም፣ ከራሣቸው በተግባር የተረጋገጠ ያለፈ ታሪክ እና በዓለም ዙሪያ እነኝኽ ድርጅቶች በሚመሩበት ፍልሥፍና፣ በሚከተሉት እምነትና በያዙት የአደረጃጀት ዘይቤ ያለፉ ኃይሎች ከተጓዙበት ሂደት ከተገኘ ልምድ፣ በእነኝኹ ቡድኖች ከደረሰ ጮክ-ብሎ ከሚጣራና ደምቆ ከሚታይ ዘግናኝ የቅርብ ጊዜ ተመክሮና በመስክ ላይ ከአለው ያፈጠጠ ሃቅ በመነሣት ነው። 'አሁን ዝም በሉ፣ እመኑን በኋላ ታዩታላችሁ' ዓይነቱን ባዶ ቃል መቀበል የማያስችለውም እነኝኽ ኃይሎች ያ ከአሁን በፊት ባገኙት ጥቂት አጋጣሚ በዜጎቻችን ላይ ያደረሱት እልቂትና ከባድ ሰቆቃ እንደገና እንዲደገም፣ ያውም በእኛው ታግዘው፣ ስለ-ማንፈልግ ነው።

ይኽን ግብዝ አካሄድ መቃወሙ የዜግነት ኃላፊነት ሆኖ ሊወሰድ ይገባል። በኋላ-ቀር ጎሠኛ የልዩነት አስተሣሰብ መርኆ ላይ የቆሙ ቡድኖችን ከራሣቸው ያለፈ የጥፋትና የውድመት ታሪክ ላይ ተመርኩዘን ከእነሱ ጋር የሚደረግን “ትብብር” መቃወሙ እምኑ ላይ *“ወደ-ኋላ ያየ”* ሊባል እንደሚችልም አይገባኝም። ተቃውሞውማ እንዲያውም ሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን ላይ ቆሞ ወደ-ኋላ ርቆ ሄዶ አጥንት ቆጥሮ ከሚከፋፍልና በሕዝብ የጋራ ጥቅሞችና ትሥሥር ላይ ስለት የሚሣርፍ አመለካከት እንጂ እንደ-አንድ አገር ዜጋ አስቦ፣ በአንድነት ቆሞ፣ ፍትኅና እኩልነትን አስገኝቶ፣ ተከባብሮ፣ ተደጋግፎና የጋራ ጥቅሞቹን አስከብሮ መኖር ሊሆን አይችልም።

“አልሰሜን ግባ በለው” ይሆናል እንጂ በአንድነቱ የዴሞክራት ኃይልማ እንዲያውም ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ባሻገር ያዩ፣ ለጋራ ጥቅምና የተሻለ ሥርዓት ይበጃሉ ተብለው የታሰቡ አማራጮች ያልቀረቡበት ጊዜ የለም። ከኢዴኃቅ እስከ ቅንጅት ከዚያም ወዲኽ ባልተቋረጠው የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግል አማራጮች በግልጥ ቀርበዋል። ይልቅስ በዚኽ ሃያ ዓመታትን ያስቆጠረ የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት የጋራ ትግል 'የእኔ አስተዋፆ ምን ነበር?' የሚለውን ጥያቄ  ነው ጥያቄውን የሚያቀርቡ ወገኖች እራሣቸውን ሊጠይቁ የሚገባ የሚመስለኝ። በእርግጥ የደሞክራቱ የአንድነት ኃይል የተሟዘዘ ይዞታና አቅጣጫ-የሣተ አካሄድ ብዙ ወገኖችን አለማስደሰት ብቻ ሣይሆን በእጅጉ አሣዝኗል፣ አነድሟልም። ያ ኒዳማ ግን “የሚሰጥም ድንጋይ ያቅፋል” ዓይነት ውድቀትን አፋጣኝ፣ እራስንም ለባሰ አደጋ የሚሰጥ እርምጃ ወደ-መውሰድ ሊያሸጋግር አይገባም። ቤት ጎደፈ ተብሎ አይቃጠልም። የሁላችን ቤት የሆነችው ኢትዮጵያችን ብልሹ ሥርዓቶች ባተረፉልን የፍትኅ እጦት፣ የእኩልነት አለመኖር፣ ረሃብ፣ ችግር፣ ኋላ-ቀርነት ወዘተ.. መጉደፏን አሌ የሚል አይኖርም። መፍትሔው ግን እነዚያን አፋኝና ኋላ-ቀር ሥርዓቶች ያተረፉልንን ጉድፎች አፅድቶ ለሁሉም እንዲመች ማድረግ እንጂ ማፍረስ አይደለም። ታዲያ ግማሹ ኢትዮጵያ የምትባለዋን የጋራ ቤቱን ለሁሉም ኗሪዎች የተሻለች እንድትሆን የየአቅሙን ሲያደርግ ሌላው ከጎን ወጋግራውንና ጣራውን ላፍርስ ሲል 'አይሆንም' ማለት ሲያንስ ነው። ከእኔው ጀምሮ አገራችን ለሁሉም ዜጎቿ መመኪያ እንድትሆን የማያስብ፣ አንድነቷን በቀናዒነት የማያይ እና በጋራ ኀልውናችን ላይ የሚሸረብን ሴራም ሆነ የሚቃጣን አደጋ ለመከላከል ወደ-ኋላ የሚል ኢትዮጵያዊ ይኖራል አልልም። የጋራ ኀልውናችን ተጠብቆ ሕዝባችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይል እምነቱን እንዲያሾርና ሠልፉን እንዲያሣምር በርካታ ድርጅቶች በልዩ ልዩ ጊዜያት አሣቦችን ሠንዝረዋል፣ ጥሪዎችን አቅርበዋል። በዚሁ መሥመር እኔም እንደ-አንድ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ “ኢትዮጵያ ከዚኽ ወዴት?” በሚለው ርዕስ ሥር ከቁጥር ሃያ-አምስት ጀምሮ የአዎንታዊ ለውጥ ፈላጊውን ክፍል የኃይል አሠላለፍ በተመለከተ ቢሆን ይሻላል ብዬ የማስበውን ዝርዝር አሣብ አቅርቤአለሁ።

ሰ) “*ይኽ እርምጃ ደፋር፣ አግባይነት የሌለውና አርቆ-ያየ ነው”፤ አልፎም “ቀስ-በቀስ መቀራረብ ከተፈጠረ እኛ በምናስበው መልክ ችግራቸውን በኢትዮጵያ አገራዊ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲፈታ ለማድረግ ቃል አስገብተናቸዋል”*፡- “ደፋርነቱ” ከምን አቅጣጫ እንደሆነ ቀደም-ሲል ስለ-ጠቀስኩት አልመለስበትም። ይሁንናም ይኽ *“አግባይነት የሌለው ትብብር”* ከአግባይነትም የአገርንና የሕዝብን ዘላቂ ጥቅሞችም ሆነ ይኽ አካሄድ የሚያስከትለውን አደጋ ቁጥር ውስጥ ያላስገባና በተፈጥሮ ባኅሪው የአንድነት ኃይሉን የግድ ያገለለ አካሄድ ነው። አልፎም የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ በተግባር የገለጠውንና የሚፈልገውን አንድነት የሚሸረሽር አካሄድ ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ ዘጠና-ሰባት እንኳን ከኢሕአዴግ በውስጡ አሥራ-አምስት ድርጅቶችን ካቀፈው ኢዴኃን

(ኅብረት) ይበልጥ አዲስ የተቋቋመውንና የስድስት ወራት ዕድሜ ብቻ የነበረውን ቅንጅት የመረጠው እነ-ኦነግ፣ ሕወሓት፣ ኦብነአግ፣ ወዘተ.. ከያዙት ሕዝብን ወደ-ኋላ ካየ ከፋፋይ ጎሠኛና ጎጠኛ አስተሣሰብ ይልቅ እኩልነቱን ሊያረጋግጥለት የሚችል አማራጭን በመፈለጉና አንድነቴ ይሻለኛል ብሎ ስለ-ተቀበለ ነው:: ስለ-ሆነም ይኽ አካሄድ ምርጫ ዘጠና-ሰባት የፖለቲካ ጎሠኝነትንና ሕዝብ ከፋፋይ ፍልሥፍናን የቃሪያ ጥፊ ያቀመሰና የሕዝብ ፍላጎት አንድነቱ እንደሆነ የማያዳግም ምላሽ የሰጠ እንደ-ነበር የረሣ ነው::

በፖለቲካ ፍልሥፍናም ይሁን በአደረጃጀት ዘይቤ ከሚቀርባቸው ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር አብረው መሥራት ያልቻሉ እነዚኽ ኃይሎች በምን ተአምር ይሆን "ችግራቸውን በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ለመፍታት" የገቡትን "ቃል" አምኖ መቀበል የሚቻለው? ከላይ በ'መ' እና በ'ሠ' እንደተጠቀሰው ሁሉ "ቀስ-በቀስ መቀራረብ ከተፈጠረ እኛ በምናስበው መልክ ችግራቸውን በኢትዮጵያ አገራዊ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲፈታ ለማድረግ ቃል አስገብተናቸዋል" የሚለው አባባልም ከባዶ ምኞታዊነትም አልፎ በእጅጉ ተላላና አደገኛ መዘናጋትን የሚወልድ አስተሣሰብ ነው:: የዚኽ ዓይነት አስተሣሰብ ደግሞ አንድም እነኝኽ ክፍሎች የራሣቸውንና የደጋፊዎቻቸውን ውድ ሕይዎት በሚጠይቅ መራር የመሣሪያ ትግል ያስሠለፋቸውንና ጫካ ያስገባቸውን ምክንያት አያውቁትም፣ ትክክልም አይደለም ማለት ይሆናል፤ አለያም ሲነሱ ካነገቡት ጥያቄ "ባነሰ" ምላሽ ሊረኩ ይችላሉ ብሎ መገመት ይሆናል:: ያ ደግሞ እነኝኽ "ነፃ-አውጭዎች" ይዘውት ከተነሱት ዓላማና ከቆሙበት እምነት አኳያ ሲታይ እራስን ከማታለልና እነሱንም ዝቅ-አድርጎ ከመገመት ውጭ ሁለቱም በአንድ ጊዜ ትክክል የሚሆኑበት ምክንያት የለም::

## <u>መደምደሚያ፤</u>

## ግልጥ አጀንዳ ግልጥ አካሄድ፤

ምን-ጊዜም ትርጉም ላገኝለት ያልቻልኩት ነገር ለምን የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግሉ በእነዚኽ አናሣ አደፍራሽ ኃይሎች ቁራኛ እንደሚያዝ መፈቀዱ ነው:: የአንድነት ኃይል ነኝ የሚለው ዴሞክራት ክፍል ከእነዚኽ በፖለቲካ ፍልሥፍናም ይሁን በልዕለ-ግብ ከማይገናኙ ቡድኖች ጋር የሚከተለውን የማባበል ፖለቲካ እስካላቆመና የእነሱን ሣይሆን የራሱን ትግል ካልታገለ የእነሱን ጎልውና ከማረጋገጥና የጋራውን ትግል ከማደፍረስ ውጭ ውጤት አይኖረውም:: **ምርጫው አንድም እስካሁን በቆየው የተድበሰበሰ አካሄድ መቀጠልና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አጀንዳቸው ያልሆነ ቡድኖችን እሹሩሩ እያሉ ማሣደግና ነገ አንገት-ላንገት ለመተናነቅ መዘጋጀት፣ አለያም ለጋራ ጎልውናችንና ዕጣ-ፈንታችን፣ ለፍትኅና እኩልነት እውን መሆን በአንዲት ኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት መርኅ ተቻችሎና ተከባብሮ በጋራ መታገል ነው:: በሁለቱ ተፃራሪ እምነቶች አንፈራጦ ለመሄድና በሁለት ባላ ለመውጣት መከጀሉ አያዋጣም::**

አንዳንድ ወገኖች በተለይም የዚኽ "ትብብር" ፈጣሪዎች በአንድ በኩል "ትብብር የግብ አንድነት/ተመሣሣይነት በአላቸው ድርጅቶች መኻልም ቢሆን ሲሠራ አላየንም፤ ስለዚኽ ወያኔን ለመጣል ከሚታገሉ ጋር ሁሉ መተባበሩ አስፈላጊ ነው"፣ በሌላ በኩል ደግሞ "ቅድሚያ ለነዚኽ ቡድኖች የሰጠነው ከአንድነት ኃይሉ ጋር ለመሥራት ምን-ጊዜም ችግር ይኖራል ብለን ስለማናስብ መጀመሪያ እነሱን ማቅረቡ ይሻላል ብለን ነው" የሚል ትርጉም የለሽ ማሣመኛ ሲሰነዝርም ተደምጧል:: የሆነ-ሆኖ ቀደም-ሲል እንዳልኩት ክርክሩ ከነዚኽ ኃይሎች ጋር ግንኙነት ጨርሶ መደረግ የለበትም የሚል ባይሆንም ቢያንስ ካለፈው ልምድና ከነዚኽ ቡድኖች ታሪክ በመነሣት ከእነሱ ጋር የሚደረግ ኃላፊነት የጎደለው የይድረስ የይድረስ "ትብብር" በተለይ በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ የሚያስከትለውን መዘዝ ከመገንዘብና ቅድሚያም ሊሰጠው የማይገባ በመሆኑ ነው:: ግንቦት-ሰባት ይሁን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚልና ለአገሪቱ አንድነት፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነት፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን እታገላለሁ የሚል ድርጅት አገራችን ባለችበት ሁኔታ ከነዚኽ ኃይሎች ጋር "ትብብር" ልፍጠር ከማለቱ በፊት የሚከተሉትን መሠረታዊና ቀላል ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርበታል::

አንደኛ የአንድነትና ዴሞክራት ኃይሉ ለሥርዓት ለውጥ የሚያደርገው ቀጣይ ትግል እስካሁን ግቡን ያልመታው እነዚኽ ኃይሎች ስላተጨመሩ ነወይ? ሁለተኛ የእነዚኽ ኃይሎች ግልጥና ይፋዊ ዓላማና ግብ ከአንድነትና ከዴሞክራሲ ኃይሉ ልዕለ-ግብ ጋር ያለው ዝምድና፣ አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው? ሦስተኛ የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሉ እንዲለወጥ በሚታገለው ሕወሓት/ኢሕአዴግና በነዚኽ ኃይሎች መኻል ያለው መሠረታዊ የፖለቲካ ፍልሥፍና ልዩነት ምንድን ነው? አራተኛ እነዚኽ ኃይሎች ከኢሕአዴግ ጋር መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ ፍልሥፍና ልዩነት ስለ-ሌላቸውና ያለያያቸው ደግሞ በጥሬው ሲቀመጥ ኢሕአዴግ "ከቸራቸው" ይበልጥ እንፈልጋለን

ብለው ስለ-ሆነ፣ ድኅረ-ኢሕአዴግ በምትኖረው ኢትዮጵያ ያንን ጥያቄና ፍላጎት ለመቀበልና ለማሟላት ዝግጁ ነኝ/እችላለሁ ወይ? አምስተኛ ከዚሁ ተያይዞ ያንን ተፈጻሚ ለማድረግ ካልቻልኩ እነዚኽ ኃይሎች ለምን ብለው ነው ከኔ ጋር ለመተባበር የሚሹት? የትብብሩስ የቅርብ-ጊዜ ዓላማ ከአገር-ወዳድና ዴሞክራት ክፍሉ ልዕለ-ግብ ጋር ይጣጣማል ወይ? ስድስተኛ ያንን እነሱ የሚፈልጉትንና ጫካ ድረስ ገብተው የሚታገሉበትን ዓላማ ለመፈጸም እንደማንችል ወይም እንደማንቀበለው እነሱም አውቀውና ተቀብለው ነው አብረን ለመሥራት የወሰንነው የሚባል ክርክር እንዳይቀርብ ደግሞ ያንን ለማሟላት ምንም ቅም-የማይለውና ይበልጥም በፖለቲካ ፍልሥፍና ከሚቀርባቸውና በተግባርም ያሣያቸው፣ ብቅ-ጥልቅ በሚል መልክም ይሁን እንጂ ከነሱ ጋር ያላቋረጠ ድርድር ከሚያደርገው ኢሕአዴግ ጋር ማድረጉ አይቀላቸውም ወይ? ወይም መጀመሪያውኑ ወደ-ጫካ ከመለሣቸው ጥያቄ ያነሰ ለመቀበል ዝግጁ ናቸው ማለት ሊሆንስ አይችልም ወይ? ያ ከሆነ ደግሞ ለዚኽ-ለዚኽ ጫካ መግባትና ደም ማፍሰሱና መፋሰሱ ለምንድን ነው?

እነዚኽ ኃይሎች በኢትዮጵያ ስም ከሚቀሣቀሱ ክፍሎች ጋር ከሚደረግ “መተባበር” አንዳችም የሚጎዱበት ጎን የለም:: ከዚኽ “ትብብር” ኪሣራን የሚሸከመው ክፍል በኢትዮጵያ ስም የዚኹ “ትብብር” አካል የሚሆኑ ወገኖች ይሆናሉ:: የሚያሣዝነው ግን የሚደርሰው ኪሣራ በእነዚኽ ድርጅቶች የሚወሰን ሣይሆን በዴሞክራሲና የአንድነት ኃይሉ የጋራ ትግል ኪሣራና በአገራችን መጻዒ-ዕድል ላይ ጭምር ሊሆን መቻሉ ነው::

ከቡድኖቹ መሠረታዊ ፍልሥፍና፣ እምነትና አሠላለፍ አብሮ መታሰብ ያለበት ቁም ነገር በመስክ ላይ ያሉ ሁኔታዎች አደገኝነት ነው:: የራሱን የሥልጣን ዕድሜ ያለ-ተቀናቃኝ ለማራዘም ካለው ጠባብ እምነት የተነሣ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በሚከተለው የአፈና ሥርዓት ምክንያት ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ሊሆን የሚችልም ሆነ አገር-አቀፍ ይዞታ፣ ተደማጭነትና ተቀባይነት ያለው ጠንካራ የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይል በሌለበት በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ከነዚኽ ፀረ-አንድነት ቡድኖች ጋር የሚደረግ “ትብብር” የሚኖረው አስተዋፅዖ ካለ ለአገዛዙ ዕድሜ-ቀጣይ መሆንና የሕዝባችን ሰቆቃ እንዲቀጥል ማድረግ ይሆናል፡፡ እንደዚኽ ዓይነት ከፀረ-አንድነት ቡድኖች ጋር የሚደረግ “ትብብር” ትዝብት-አይፈሬ ለሆኑት የአገዛዙ ቁንጮዎች 'የአገር-አንድነትን ከተገንጣዮች ለመከላከል' የሚል የመዛበቻ ሁኔታንም ይፈጥርላቸዋል፡፡ አልፈውም ማዕከላዊነትና አገራዊ አንድነትን ከነሡ ሥልጣን ላይ መቆየት ጋር ለማዛመድና ለማስተሣሰር በሚያደርጉት መሠሪ አካሄድ የኢትዮጵያን እንደ-አገር የመቀጠልና ያለ-መቀጠል ጉዳይ በወለድ-አገድ መያዣ ሊያደርጉትና ሊቀጣጠቡበት ከአሁኑ እየተንደረደሩ እንደሆነም እየታየ ነው::

በአገራችን ያለው ሁኔታ ለለውጥ ከቆመው የአንድነትና የዴሞክራሲ ይዞታ ጋር ሲነጣጠር ምናልባትም የኢትዮጵያ መጻኢ-ዕድል ልክ የዛሬ ከሃያ ዓመት (በሰማንያ-ሦስት ዓ/ም) ለንደን ላይ ያ የአንድነት ኃይሎችን ጨርሶ ያገለለና በባዕዳን ኃይሎች አቀናባሪነትና አስተናባሪነት አማካይነት ሦስት ከአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅምም ይሁን ክብር ጋር ትውውቅ በሌላቸው ኃይሎች፣ ማለት በሸዓብያ፣ ሕወሓትና ኦነግ፣ እንደተወሰነው ሁሉ፣ አሁንም የኃይል አሠላለፉ ይኸንኑ አደጋ የሚጋብዝ እንደሆነ ልብ ይሏል:: ተቃውሞ የምናሰማ ወገኖችን የምር የሚያሣስበንም አንዱ ከዚኹ ሃቅ በመነሣት ነው::

የአሁኑ “የትብብር” ቅኝት የኢትዮጵያን ችግሮች በሥልጣን ላይ ካለው ቡድን ውጭ ማየት ላልቻሉ አንዳንድ አገር-ወዳዶች የእርጎ-ባሕር ያሣየና ብዙዎችንም ሊያነሆልል የሚችል፣ ቆይቶ ግን በፀፀት ወደ-ማይመለስ ስህተት ውስጥ የሚያስገባ ድርጊት መሆኑ ግልጥ ሊሆን ይገባል:: የዚኽ “ትብብር” ሌላው የቅርብ-ጊዜ ጉዳት ደግሞ አገዛዙ የነኻኽን ቡድኖች እንቅስቃሴ ምክንያት በማድረግ 'በፀረ-አንድነት ኃይሎች ላይ የሚደረግ ግዳጅ' በሚል ሰበብ አፈናውን እንዲያጠናክር ዕድል ይሰጣል:: ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም በነዚኹ ቡድኖች ፀረ-አንድነት አቋም ላይ ባለው ስጋት ምክንያት አገዛዙን ለማስወገድ የሚያደርገውን የጋራ ትግል በሙሉ ልቡ እንዳይገፋበት የተወሰነ ጫና ያሣድራል:: አገር-ወዳዱንና የአንድነት ኃይሉንም እንዲከፈልና እንዲዳከም ያደርጋል:: ይኸም በመሆኑ በዚኽ የሁለት አናሣ ኃይሎች (በአገዛዙና በእነዚኽ ቡድኖች) ተደጋጋፊ መሣሣብ ምክንያት አገሪቱና ሕዝቧ ላይ ያለው የችግር አዙሪት እንዲቀጥል ይሆናል ማለት ነው:: ይኽ አደጋ ደግሞ ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ እስከ-ሌለ ድረስ የሚዘልቅ ነው::

የነ-መለስ ጎሠኛ ርዕዮት ኢትዮጵያውያን እንደ-ኢትዮጵያዊ እንዳያስቡ ከአጠቃላዩ (ከወሉ) ይበልጥ ሁሉም የየግል ጎሣውን መታወቂያ እንዲያጠብቅና ብሔራዊ ስሜትን በብሔረሰበኝነት በመተካት በመኻላቸው ዘላቂ ውጥረት እንዲፈጠር አስልተው ስፖርትን ሣይቀር “የአማራ ክልል፣ የኦሮሞ፣ የሐረሪ፣ ወዘተ ” በሚል “ማወዳደር” መጀመሩ ይታወቃል:: የዚኽ ዓይነት ኋላ-ቀር የአደረጃጀት ዘይቤ የሚያስከትለውን አደጋ ባለ-መገንዘብ ይመስላል በዚኽ “ወያኔን እናስወግድ” ግልብ ዘመቻ የተጠመዱ አንዳንድ ወገኖችም “የኦሮሞ ወጣት፣ የአማራ ወጣት፣ ወዘተ..” በሚል ጎሠኝነትን መሠረት ባደረገ ተመሣሣይ አፈረጃጀት “የትግል አንድነት” እንዲኖርና ሕዝባዊ

መነሣሣት እንዲቀሰቀስ እየደከሙ እንደሆነ በጽሑፍ ሣይቀር እያየን ነው:: እግዚአብሐር ያሣያችሁ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲነሣሣ ከሆነ የሚፈለገው በተለይ ተረካቢውን ወጣት ትውልድ እንዲኽ በጎሣ ለመፈረጅ ማሰቡ የጤና ነው? ዓላማውስ ምንድን ነው?

በዚኽ "ወያኔን ብቻ እናስወግድ" ግልብ አስተሣሰብ ፀረ-አንድነትና የመገንጠል አጀንዳ በግልፕ ካነገቡ ጋር የሚደረግ "ትብብር" ከመነሻው መቸነፍን ተሸክሞ የሚጓዝ በመሆኑ ለድል የሚያበቃና ግብ-አስጨባጭ አካሄድ አለመሆን ብቻ ሣይሆን ተቃዋሚውን ክፍል አንድ እርምጃ ወደፊት ሦስት እርምጃ ወደ-ኋላ የሚወስድና የአገር አንድነትንም ለአደጋ የሚጋብዝ ነው:: ይኽ "የጠላቴ ጠላት" ሠልፍ አንዳንድ ወገኖችን የባዕዳን መሣሪያ እንዲሆኑ እያመቻቸ እንደሆነም የታወቀ ነው:: የዚኽ "ትብብር" ውጤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለአዎንታዊ ለውጥ የሚታገለውን ክፍል አቅጣጫ ለሣተና ለአላስፈላጊ ክፍፍል መዳረግ፣ በሁለተኛ ደረጃ  በቅርቡ ትግሉን የሚያወሣስብ ብቻ ሣይሆን የኢትዮጵያውያን የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግል የሚያሰናክል፣ ሦስተኛ በአገራችን ኀልውና ላይ አደጋን የሚጋብዝ እርምጃ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፥ ይኽ "ትብብር" ዓላማው "የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ብቻ" ያለመ የቅርብ (የአጭር) ጊዜ ግብን ያነገበ ነው የሚል "ማስተዛዘኛ" ሲነገርም ተደምጧል:: ማንኛውም የአጭር ጊዜ እርምጃ ውጤት አስገኝ ትብብር ለሁሉም የትብብር-ፈጣሪ ክፍሎች እኩል ውጤት ላይሰጥ ይችላል፤ ለአንዱ ወይም ለተወሰኑ ክፍሎች ለዕለ-ግብ ቁልፍ እርምጃ ወይም ወሳኝ መረማመጃ ሊሆን ሲችል ያው ተመሣሣይ እርምጃ በተቃራኒው ለሌላው ወይም ለሌሎቹ ክፍሎች እና እነሱም ለቆሙባቸው በይፋ የሚነገሩ ዓላማዎች ቀብር-ቆፋሪና አክሳሚ ሊሆን እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል:: ተቃውሞውም የተያዘው የኃይል አሠላለፍ የተጠቀሰውን የቅርብ (የአጭር) ጊዜ ግብ በማስገኘቱ የሚገታ ሣይሆን የረጅሙን ጊዜ ዓላማ (ልዕለ-ግብ) በአሉታዊ መልኩ ሊወስን የሚችልበት ዕድል ስላለው ነው::

እስካሁን ድረስ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ ኃይሎች መኻል የሚደረግ የትብብር ሙከራ ሁሉ የተፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለበት አንዱ ምክንያት ደግሞ በቀጥታ የሚያያዘው የኃይል አሠላለፉን ተፈጥሮ መሠረት ያደረገ እንደ-ሆነ ሊዘርነጋ የሚገባው ጉዳይ አይመስለኝም::

በአገራችን ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት ለውጥ ለማስገኘት የመጀመሪያው እርምጃ መቻቻልና መከባበርን፣ ሁሉም በዚያች አገር በእኩልነት የመኖር መብት ያለው መሆኑን እና የአገራችን አንድነት ለችግሮቻችን ተጠያቂም ምክንያትም እንዳልሆነ መቀበል ይመስለኛል:: ለዚኽ ደግሞ ዜጎችን በጠላትነት የሚፈርጅና የሚከፋፍል የፖለቲካ ኀሠኘነትን ማስወገድ የግድ ይላል:: አንዳንድ ወገኖች ከአገዛዙ በኩል ያለውን እንጂ ከዚያ ውጭ በተቃዋሚው ጎራ የሚታየውን ፖለቲካዊ ኀሠኘነት ላይ የተመሠረተን የኃይል አሠላለፍ ጠንቅ አቅልሎ ማየትን የመረጡ ይመስላል::

ሐይማኖትን፣ ዘርንና ጎሣን መሠረት ያደረጉ የፖለቲካ አደረጃጀቶች በእጅጉ አግላይና አባላቱም ተፈጥሮን ተጋፍተው "እነሱን ያልመሰለውን" በጭፍን ጥላቻ እንዲያዩ የሚያደርጉ በመሆናቸው፣ አብረው "አፈር እየፈጩ፣ ውሃ እየተራጩ" የኖሩ ቅርብ አብሮ-አደግ ጓደኛሞችና ጎረቤቶች ሣይቀር ከመ-ቅጽበት እንደማይተዋወቁ አንዱ የሌላው መራር ጠላት ሆኖ እንዲተራረዱ የሚያደርግ "ሰይጣናዊ" አስተሣሰብን በሰዎች አእምሮ የሚወልድ አደገኛ መሆኑ በዓለም ዙሪያ በተደጋጋሚ የታየ አሣዛኝ ጉዳይ ነው:: ስለ-ሆነም በደፈናው *"የጋራ ጠላትን ለማስወገድ"* በሚል በዚያ መሥመር ከተደራጁና ግልጥ ፀረ-አንድነት አጀንዳ ካነገቡ ታጣቂ ክፍሎች ጋር ማንነታቸውንና ትክክለኛ ድርጅታዊ ተፈጥሮአቸውን ምንም ሊለውጥ የማይችልን የእነሱኑው ባዶ የቃል ተስፋ ብቻ ይዞ የሚደረግ "ትብብር" ቢያንስ 'አሣ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ' ከመሆን አይዘልም::

ዓላማችንና ፍላጎታችን አገራችንን ከትርምስ ማዳንና ሕዝባችንም የራሱ ዕድል ወሣኝና ፍትኅንና እኩልነትን ለሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ከሆነ፣ አሠላለፋችን እንደ-እምነታችን በኢትዮጵያና በኢትጵያዊነት ላይ የቆመ፣ አጀንዳችንም በግልጥ ይኸንኑ የሚያንፀባርቅ ሊሆን ይገባል::

የነገውን ሣይሆን የአሁኑን አይቸ
ክረምት መምጣቱን ጨርሶ ዘንግቸ
ቆሸሸብኝ ብዬ ማፅዳቱን አጥቸ፣
ቤት-አልባ ሆኛለሁ ቤቴን አጋይቸ::

**… አለ ተፀፃች!**

**ኸረ እየተስተዋለ፣ ወገን!!**

**አንድነት ኃይል ነው!! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**